# <u>የተሻሻለውን የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ረቂቅ አዋጅ አስመልክቶ የቀረበ አስተያየት</u>

ተሻሽሎ የቀረበው ረቂቅ አዋጅ ቀደም ሲል ያቀረብናቸውን አስተያየት ያካተተ በመሆኑ አድናቆታችን ከፍ ያለ ነው፡፡ ቀደም ሲል ያቀረብናቸው ሃሳቦች እንደተጠበቁ ሆነው አሁን በተሻሻለው ረቂቅ አዋጅ ላይ የሚከተለውን አስተያየት እያቀረብን እንደተለመደው ሁሉ ተገቢውን ማስተካከያ እንደሚደረግ ባለሙሉ ተስፋ ነን፡፡

## 1. አንቀጽ 2 ትርጓሜን በተመለከተ

ቀደም ሲል በተደጋጋሚ እንደገለጽነው የገቢ ምንጭ የበጐ አድራጐት ድርጅቱን ማንነት ሊመዝን የሚገባ መለኪያ መሆን የለበትም የሚል እምነት አለን፡፡ በዚህ ጉዳይ ሕገ መንግሥታችንንና መሠረታዊ የሕግ መርሆችን አጣቅሰን የበኩላችንን አስተያየት ሰጥተናል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አሁን በተሻሻለው ረቂቅ አንቀጽ 2/4/ “የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የበጐ አድራጐት ድርጅት” ወይም “የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ማህበር” የሚለው ትርጉም ዜጐችን ወደ ነዋሪነት ዝቅ የሚያደርግ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የዜግነትና የነዋሪነት መብት በእጅጉ የተለያዩ ናቸው፡፡ ዜጐቻችን መኖሪያቸው የትም ይሁን የት የመደራጀት መብታቸው የተከበረ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህ ትርጓሜ ግን በነዋሪነት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ኢትዮጵያዊያን የዜግነት መብት ከማሳነሱም በላይ ነዋሪ መሆንን የሚጠይቅ በመሆኑ ከኢትዮጵያውያን ይልቅ በኢትዮጵያ ለሚኖሩ የውጭ ሃገር ሰዎች የሚስማማ ነው፡፡ ስለዚህ የዜጐችን መብት በሚጠብቅ መልኩ እንዲስተካከል እንጠይቃለን፡፡

- “የሥራ መሪ” ለሚለው ቃል የተሰጠውን ትርጉም የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ይቻል ዘንድ… “የበጐ አድራጐት ድርጅቱን ወይም የማህበሩን <u>የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ</u> … በበላይነት የሚቆጣጠር እና የሚመራ ሰው ነው፡፡” በሚል ቢተካ

በተጨማሪም በተሻሻለው ረቂቅ ሕግ ውስጥ ለሚከተሉት ግልፅ የሆነ ትርጉም ቢካተት ለአፈፃፀም የተሸለ ይሆናል፡፡

- “የውጭ ገንዘብ”
- “ፕሮግራም ወይም የፕሮጀክት ስራ”
- “አስተዳደራዊ ወጪ”

2. አንቀጽ 3 የተፈፃሚነት ወሰን

በዚህ አንቀጽ 3/2/ ሥር ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የሚከተሉት ቢጨመሩ፡-

- አህጉራዊ ባህርይ ባላቸው ጉዳዮች ላይ በሚሰሩ
- በልዩ ባሕርያቸው ምክንያት በሌላ ሕግ የሚሸፈኑ ማህበራት

3. አንቀጽ 6 የኤጀንሲው ሥልጣን

- ንዑስ ቁጥር 1/ሀ/ … የማህበራት ፈቃድ መስጠት፣ ማደስ፣ መመዝገብና መቆጣጠር ተብሎ ቢስተካከል
- ንዑስ ቁጥር 1/ቸ/ ወሰን የሌለው ሥልጣን የሚሰጥ ስለሆነ ቢወጣ

4. አንቀጽ 8 የቦርዱ አባላት

ተጨማሪ ንዑስ አንቀጽ ቢኖር በዚህም መሠረት

- በተጨማሪም ከበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት ተመጣጣኝ ቁጥር ያላቸውና በራሳቸው በድርጅቶቹና ማህበራቱ የሚመረጡ ተወካይ የቦርድ አባላት ተብሎ ቢስተካከል

5. አንቀጽ 9 የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ን.አ.2 በበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት አስተዳደር ላይ ጣልቃ ገብነትን የሚጋብዝ በመሆኑ ቢወጣ፣

6. አንቀጽ 14 የበጐ አድራጐት ድርጅት

6.1 በንዑስ አንቀጽ /ተ/ እና /ቸ/ የፆታና የሕፃናት ጉዳይን አስመልክቶ የተቀመጠው በቀድሞው ረቂቅ መሠረት ቢሆን፣

6.2 "የሐይማኖት እኩልነትና መብትን ማረጋገጥና ማበረታታት" የሚለው ሃረግ ከመሠረታዊ የሰው ልጆች መብት እና ከሕገ መንግሥቱ መንፈስ ጋር የሚጋጭ በመሆኑ በ14.5 የተቀመጠው ገደብ ቢወጣ፡፡

የሚከተሉት ተጨማሪ ተግባሮች በአንቀጽ 14 ከተዘረዘሩት የበጎ አድራጎት ዓላማዎች ውስጥ ቢካተቱ፣

- የአርብቶ አደሩን ሕይወት የሚለውጡ ጥረቶችን ማስፋፋት
- በተለያዩ መስኮች ምርምርና ጥናት ማድረግ፤ የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት እና መረጃን ማሰራጨት፣
- ሴቶችና ሕፃናት የሚደርስባቸውን ማናቸውም የማህበራዊ ችግሮች መርዳትና መንከባከብ፣

7. አንቀጽ 15 /3/ እንደሚከተለው ቢስተካከል

የበጐ አድራጐት ድርጅቶች ስራቸውን የሚያስተባብር፣ አቅማቸውን የሚገነባ፣ መብታቸውን የሚያስጠብቅ እና በሁለንተናዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ድምፅ የሚያሰማ ወዘተ… የበጐ አድራጐት ድርጅት ሕብረት /ጥላ/ ማቋቋም ይችላሉ፡፡

8. አንቀጽ 48 ግልፅነት የጐደለው ስለሆነ በደንብ ቢብራራ

9. አንቀጽ 56 በሚከተለው መልኩ ቢስተካከል

56/1/ በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱት የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች በሌላ አዋጅ ስለሚተዳደሩ ከዚህ ቢወጡ፡፡

56/2/ ማህበራት ሥራቸውን የሚያስተባብር እና በጋራ የቆሙለትን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችላቸው ሕጋዊ ሰውነት ያለው የማህበራት ሕብረት /ጥላ/ ማቋቋም ይችላሉ በሚል ቢስተካከል፡፡

10. አንቀጽ 58/1/ የማህበራትን የውስጥ ነፃነት ስለሚጋፋና ድግግሞሽም ስለሚሆን ቢሠረዝ እና የተሸለ አገላለፅ ባለው በአንቀፅ 58/4/ ቢተካ።

11. አንቀፅ 58/6/ - ላይ የሰፈረው ሃሣብ እጅግ ገዳቢ ስለሚሆን፣ በፌደራል ደረጃ መንቀሳቀሱ በማህበሩ ራዕይና አላማ፣ የሥራ ባሕርይ፣ የገንዘብ አቅምና የአሰራር ስትራቴጂ እንዲሁም ለወደፊት የማደግ ዕቅድ ላይ ብቻ የተመሠረተ ሊሆን ስለሚገባ ቢወጣ ወይም በዚሁ መሠረት ቢስተካከል፣

12. አንቀጽ 58/3/ እንደሚከተለው ቢስተካከል፡-

"ማንኛውም ማህበር መደበኛ አባላት፣ ተባባሪ አባላት እና የክብር አባላት ሊኖሩት ይችላል። ድምፅ የሚሰጡት ግን መደበኛ አባላት ሲሆኑ እነሱም እኩል የሆነ ድምፅ አላቸው"

13. አንቀፅ 58/5/ ላይ "..... በስራ አስፈፃሚው የመሰማት መብት አለው" የሚለው "በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው" በሚል ቢስተካከል።

14. አንቀፅ 59/2/ - ጠቅላላ ጉባዔ፣ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና <u>የውስጥ</u> ኦዲተር በሚል ቢስተካከል፣

15. አንቀጽ 60 ሥር የሚከተለው ሃሳብ በተጨማሪ ቢካተት
"በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ጠቅላላ ጉባዔው የማህበሩ የበላይ እና የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ አካል ሆኖ የማህበሩን ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ/ቦርድ/ አባላትን ይመርጣል፣ ያግዳል ያሰናብታል።"

አንቀፅ 60/2/ በሚከተለው ቢተካ፡-
"በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የማህበሩን የውጭ ኦዲተር ይመርጣል፣ ያሰናብታል፣ የክፍያውንም ጣሪያ ይወስናል።"

አንቀፅ 60/5/በሚከተለው ቢተካ ፡-

“የማህበሩን ቅርንጫፎች መክፈትና መዘጋት እንዲሁም የማህበሩን መፍረስ ይወስናል፣”

16. አንቀፅ 62/2/ በሚከተለው ሃሳብ ቢተካ፡-

“በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ሰብሳቢው በቂ ባልሆነ ምክንያት በ30 ቀናት ውስጥ ስብሰባ ያልጠራ ከሆነና ለመጥራትም ፍቃደኛ ካልሆነ 1/3ኛ የሚሆኑት አባላት ለኤጀንሲው በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ስብሰባውን እንደጠራ ወይም ያልጠራበትን ምክንያት እንዲያስረዳ ኤጀንሲው የማህበሩን ሰብሳቢ ሊጠይቀው ይችላል፡፡”

አንቀፅ 62/3/ እንደሚከተለው ቢጨመር፡-
“ኤጀንሲው ስብሰባው ያልተጠራበትን ምክንያት መርምሮ ስብሰባውን ላለመጥራት በሰብሳቢው የቀረበው ምክንያት በቂ ሆኖ ካላገኘው በ30 ቀናት ውስጥ ስብሰባውን እንዲጠራ ሊያዘው ይችላል፡፡”

የቀድሞው 62/3/ ንዑስ ቁጥር 4 ሆኖ እንደሚከተለው ቢነበብ፡-
“ሰብሳቢው በኤጀንሲው በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ስብሰባውን ባይጠራ በኤጀንሲው አማካይነት የጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡”

አንቀጽ 62/3/ ንዑስ ቁጥር 5 እንደሚከተለው ቢነበብ፡-
“የጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ የተጠራው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /4/ መሠረት ከሆነ የዕለቱን ስብሰባ ለመምራት ሊቀመንበር የሚሆን ሰው አባላቱ እንዲመርጡ ኤጀንሲው ያደርጋል፡፡”

አንቀጽ 62/4/ እና /5/ እንዳሉ ሆነው ቁጥራቸው 6 እና 7 ቢሆን

17. አንቀጽ 68/3/ እንደሚከተለው ቢስተካከል ፡-

“በማቋቋሚያ ሕጉ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሠረት የስራ እንቅስቃሴያቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ለኤጀንሲው ሪፖርት በማድረግ በኤጀንሲው በኩል ተገቢው እርምት እንዲወሰድ ሃሳብ ያቀርባል፡፡”

18. አንቀፅ 69/1/ “……. የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትና የምዝገባ ማመልከቻ በቀረበ በ30 ቀናት ውስጥ ይሰጣል” በሚል ቢስተካከል፡፡

አንቀፅ 69/2/ ተብሎ ይህ ሐሳብ ቢገባ፡-
ማንኛውም ለምዝገባ የሚቀርብ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር አስፈላጊ ሁኔታዎች አሟልቶ በቀረበ ጊዜ ኤጀንሲው ከሰላሳ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አመልካቹን በመመዝገብ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ይሰጣል ወይም ምዝገባው ተቀባይነት ያለማግኘቱን በጽሁፍ ይገልፃል፡፡

የረቂቁ አንቀጽ 69/2/ አንቀጽ 69/3/ ቢሆን፣

የረቂቁ አንቀፅ 69/2//ለ/ ለተለያዩ ክፍተቶች የሚያጋልጥና መብትና ግዴታን በግልፅ የማያመለክት በመሆኑ ቢወጣ፣

የሚከተለው አንቀጽ 69/4/ ሆኖ በተጨማሪነት ቢቀመጥ፡-
ኤጀንሲው በተጠቀሰው የ30 ቀን የጊዜ ገደብ ውስጥ ለአመልካቹ ውሳኔውን ካላሣወቀ አመልካቹ እንደተመዘገበ ይቆጠራል፡፡

19. አንቀፅ 70/5/ - ላይ የሰፈረው ሃሣብ በአንቀፅ 3/1/ እና በአንቀፅ 56/1/ ላይ ስለማህበር ከተሰጠው ትርጉም ጋር ስለሚጣረስ ቢወጣ፣

20. አንቀፅ 71/5/- ያለቦታው የተቀመጠ ስለሆነ ቢወጣ

21. አንቀፅ 72/2/ "….. በማስረጃነት ተቀባይነት ይኖረዋል" የሚለው ተሰርዞ "በማስረጃነት ሊቀርብ ይችላል" በሚለው ቢስተካከል፡፡

22. አንቀፅ 73/3/ በሚከተለው መልኩ ቢስተካከል፡
   - አንድ የበጎ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር አስቀድሞ ኤጀንሲውን ሳያሳውቅ ቅርንጫፍ ቢያቋቁም እና ከኤጀንሲው ለደረሰው የመጨረሻ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ በ30 ቀናት ጊዜ ውስጥ የማስተካከያ እርምጃ ካልወሰደ ኤጀንሲው በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

23. አንቀፅ 76/2/ - ዝርዝር ጉዳይ ስለሆነ ቢወጣ

24. አንቀፅ 80/3/ - እንደሚከተለው ቢስተካከል
    የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /2/ ቢኖርም ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ወይም በማናቸውም በቂ ምክንያት ማንኛውንም ዓይነት የሒሳብ ምርመራ በውጭ ወይም በውስጥ ኦዲተር ኤጀንሲው እንዲመረመር መመሪያ ሊሰጥ ይችላል፡፡

    ንዑስ አንቀፅ /4/ በንዑስ አንቀፅ /3/ የሚተካ ስለሆነ ቢወጣ

25. አንቀፅ 93 ፡- ከዚህ በላይ የተቀመጡት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኤጀንሲው፣ የዘርፍ አስተዳደሪው እና የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በመመካከር የአስተዳደራዊ ወጪን ከ30 በመቶ በላይ የሚሆንበትን ሁኔታ ይወስናሉ፡፡

26. አንቀፅ 91/3/፡- በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በቅጥር ላይ ያልተመሠረተን የውጭ ሃገር ሰዎች የበጐ ፈቃድ አገልግሎትን ይህ ድንጋጌ አይመለከትም፡፡

27. አንቀፅ 95/ለ/ እና /ሐ/ እንደሚከተለው ቢስተካከል

- “የበጐ አድራጐት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ፈቃድ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 94 መሠረት ሲሰረዝ እና መሠረዙ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ሲፀና”፣

- አንቀፅ 95/2/ እንደሚከተለው ቢስተካከል፡-
  “ከላይ አንቀፅ 95/1//ለ/ ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከዚህ ቀጥለው በተመለከቱት ምክንያቶች የበጐ አድራጐት ድርጅቱን ወይም ማህበሩን ሊያፈርስ ይችላል” ተብሎ ቢስተካከል

28. አንቀፅ 99/1/ ሕዝባዊ መዋጮ የሚደረገው ለኤጀንሲው አስቀድሞ በማሳወቅ ብቻ ቢሆን፣

29. ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር እና ከፍትህ ሚኒስትሩ ጋር በተደረገው ስብሰባ ላይ እንደተነገረው የሲቪል ማህበራት ገቢያቸውን በዋናነት ማግኘት የሚገባቸው ከሀገር ውስጥ ምንጮች ስለሆነ ሕዝባዊ መዋጮዎችን በማሣወቅ ብቻ ማድረጉ ድርጅቶችን ወይም ማህበራትን ገቢያቸውን በተቀላጠፈ መልኩ እንዲሰበስቡ ስለሚያስችል ነው፡፡ ስለዚህ አንቀፅ 100፣ 101 እና 102 ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ቢስተካከል፡፡

30. ምንም እንኳን በመጀመሪያው ረቂቅ ውስጥ የተዘረዘሩት አስተዳደራዊ ቅጣቶች በተሸሻለው ረቂቅ ውስጥ መቅረታቸው በጎ አካሄድ ቢሆንም አሁን ከአንቀጽ 104-108 የተዘረዘሩት ቅጣቶች ግን ከበፊቱ እጅግ የከበዱና የከረሩ በመሆናቸው አበረታች አይደሉም፡፡ ስለሆነም የሲቪል ማህበራትና ደርጅቶች ስራን አስፈሪና ገዳቢ እንዳያደርጉ ቅጣቶቹ ተመጣጣኝና አስተማሪ ሆነው ቢስተካከሉ፡፡

31. አንቀፅ 109 /1/…… “ከአላማው ጋር ተያያዥነት ያላቸው” የሚለው ገዳቢ ስለሆነ ቢወጣ፣

32. አንቀፅ 110/1/ እንደሚከተለው ቢስተካከል፣
"ኤጀንሲው ማንኛውንም በአሰራሩ ላይ የሚቀርብለትን አቤቱታ ተቀብሎ በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ መወሰን አለበት፡፡"

33. አንቀፅ 110/2/.... "ቦርዱ የሚሰጠው ውሣኔ" የሚለው ለውጭ ሃገር የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና እና ማህበራት የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል ተብሎ ቢስተካከል፡፡

አንቀፅ 110/3/.... እንደሚከተለው ቢስተካከል፡-

የኢትዮጵያ የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ማህበር በማናቸውም የቦርዱ ውሳኔ ላይ በ30 ቀን ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ መብት ይኖራቸዋል፡፡ /ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር የተደረገውን ውይይት ያስታውሣል/፡፡

34. አንቀፅ 113/1/ ..... "አግባብነት ያለው አካል" የሚለው ሃረግ ግልፅነት ይጐድለዋል፡፡

35. አንቀፅ 116/2/ ፡- ቀደም ሲል ተመዝግበው የነበሩት ሁሉም የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ይህ አዋጅ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በሦስት ዓመት ውስጥ እንደገና መመዝገብ አለባቸው፡፡

## ተጨማሪ አንቀፆች

1. ***ከማናቸውም ግብር ነፃ ስለመሆን***

የበጐ አድራጐት ድርጅቶችና ማህበራት በማህበረሰባዊ ደህንነቶች እና ጥቅሞች ላይ የሚሠሩ በመሆናቸው ከማናቸውም ዓይነት ግብሮች ነፃ ሊደረጉ ይገባል፡፡ /የሌሎች ሃገሮች ሕጐች ተሞክሮ ይህንን ያስረዳል/፡፡

2. የሃገር ውስጥ ለጋሾችን ለማበረታታትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ከውጭ ጥገኝነት እንዲላቀቁ ማድረግ ይቻል ዘንድ ለጋሾች የሚለግሱት ገንዘብ በሚያቀርቡት ማስረጃ መሠረት ከታክስ ተቀናሽ ሊሆንላቸው ይገባል፡፡

ማሳሰቢያ፡- ይህ አዋጅ በአዋጅነት የሚወጣ ስለሆነ ሌሎች የግብር ዓይነቶችን ወይንም ለፋይናንስ እና ኢኮኖሚ የተሰጠው ስልጣን የሚገድብ ወይም የሚያሳንስ እንዳልሆነ ግንዛቤ ቢወሰድ፡፡